EthioLion

# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዚያ 2001

### (ጋይም) ገብረ እግዚአብሄር ወልደ ሚካኤል
### ለሕዝብ የወደቁ ሰማዕታት ሁሌም ሕያው ናቸው

አስራ ስድስት ዓመት በፊት በግንቦት ወር 1985 ዓ.ም. የኢሕአፓ አመራር አባል የነበረው ጓድ ገብረ እግዚአብሔር ወልደ ሚካኤል (ጋይም) የድርጅት ሥራ በህቡዕ ይሠራ በነበረበት በአዲስ አበባ በአንድ ከሀዲ ተጋልጦ በወያኔ ፖሊሶችና የፀጥታ ሠራተኞች ያደረጉበትን ከበባ ለመቋቋም ሲታኮስ መስዋዕትነትን ተቀብሏል። ጓድ ጋይም ከቋራ ወደ ሱዳን ከሱዳን ደግሞ በህቡዕ ወደ አዲስ አበባ ገብቶ ከሌሎች ጓዶች ጋር የድርጅቱን መዋቅር ሲዘረጋና ሲያጠናክር ነበር።

ጓድ ጋይም የኢሕአፓ ሽምቅ ተዋጊ ኃይል ወደ አሲምባ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በሠራዊቱ ተሰልፎ በልዩ ልዩ ደረጃ ሲታገል የቆየ ሲሆን በአሲምባ በጠላት እጅ ወድቆ ወደ አሥመራ ሰምበል እስርቤትም ተወስዶ ታስሮ ሲለቀቅ ሠራዊቱን እንደገና ተቀላቅሎ በቆራጥነት የታገለ ጓድ ነበር። ጓድ ጋይም በወልቃይት በውጊያ ቆስሎ ይታከም ከነበረበት ቦታም ወያኔ ሊይዘው ችሎ ካሰረው በኋላ ከወያኔ አምልጦ ኢሕአሠን ተቀላቅሎ ትግሉን ቀጥሎ ነበር። ኢሕአሠ የብተና አደጋ ከደረሰበትም በኋላ በቀጠለው የሠራዊቱ ትግል ጓድ ጋይም ከፍተኛ ሚና ነበረው። በጎንደርና ጎጃም የሠራዊቱ ኃይል ሲጠናከርና ሲስፋፋ በመሪነት ቦታ አስተዋፅዖ አድርጓል። በከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባልነትም ታግሎ ሲያታግል የቆየ ጓድ ከመሆኑ ሌላ በፀረ ወያኔው ትግልም ድርጅቱ በጥንካሬ ለመታገል ይችል ዘንድ በህቡዕ ትግሉን በመምራት የበኩሉን ድርሻ ተወጥቶ ተሰውቷል። በወቅቱ በሽፋን ስም በነፃ ጋዜጦችና መጽሄቶች የተለያዩ የቅስቀሳ ፅሁፎችንም አበርክቷል። ጓድ ጋይምን ለወያኔ አገዛዝ ያጋለጠው ከሀዲ በባህር ዳር ከተማ ተገቢ ቅጣቱን በኢሕአፓ እጅ የተቀበለ ቢሆንም ጓድ ጋይም መሰዋቱ ለድርጅታችን ጉዳት መሆኑ የሚካድ አይደለም።

የኢሕአፓ የአመራር ኮሚቴ አባላት ሆኑ አባላቱ በአጠቃላይ ለሕዝብና ለሀገር የገቡትን ቃል ኪዳን በማክበር በጀግንነት ታሪክን እየፃፉ አልፈዋል። ተስፋዬ ደበሳይ፥ ክፍሉ ከበደ፥ ዮሴፍ አዳነ፥ ዮሐንስ ብርሃኔ፥ ፍቅሬ ዘርጋው፥ ብንያም አዳነ፥ ፀሎተ ሕዝቅያስ ...ወዘተ...ወዘተ በኃላፊነት ቦታ የታገሉ ጓዶችንና የሌሎቹንም የነ መህመድ ማህፉዝን፥ ወብሸትን፥ ዘርዓብሩክንን፥ የይትባረክን፥ የአልማዝን፥ የተካልኝን፥ የፅጌን...ወዘተ አርዓያነት ጋይምም ተቀብሎ ለሕዝብ መስዋዕት ሆኗል። ለጋይም መሰዋት ተጠያቂ የሆኑት እነመለስ ዜናዊ፥ ስብሀት ነጋ፥ ሀሰን ሺፋ፥ አራንሻና ሌሎቹም ወንጀለኞች ሁሉ በሀገርና በሕዝብ ላይ ለፈፀሙት ወንጀል ለፍርድ እስኪቀርቡና ሀገርና ሕዝብ ነፃ እስኪሆኑ ድረስ ኢሕአፓ ሰማዕቱን እየዘከረ ትግሉን ይቀጥላል።

በትግል መሞት ሕይወት፤ ዳግም ትንሳዔ ልደት!

EthioLion.com

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

Ethiopia will prevail !